




# አባባሱባት!




ወንድሙ መኰንን፣ አይልስበሪ፣ እንግላንድ መጋቢት ፲፯ ቀን ፪ሺ፭ (26 March 2013) ዓ.ም.

## መግቢያ

ሎንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን፣ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ሁሌ ጥቃት እንደተሰነዘረባት ነው። ክፉ ክፉው መዘዝ የሚመዘዝባት፣ ሁዳዴ ጾም አካባቢ ነው። በዞ አሳልፋለች። ይንከባከቧታል ተብለው ታምነው የነበሩ ትላልቅ አባቶች እየመዘበሯት ስላስቸገሩ፣ መነኩሴ አንዴ ሙቶ ተገንዟልና አደራ አይበላም ለገንዘብና ለሥልጣን አይጓጓም ተብለን ለመነኩሴ ነኝ ባዩ ግለሰብ ቢያስረክቧት፣ እንኳን ሊሻላት እንዲያውም **<u>አባባሱና</u>**፣ አረፉ። በገንዘባችን የገዛናትን ቤተክርስቲያን በሯን ጥርቅም አድርገው ዘግተው ሜዳ ላይ አፈሰሱን። ያም ብቻ አይደለም። እንደምንሰማው ከሆነ አንድ ከአዲስ አበባ ተሾመው ለመጡት፣ የታጋይ ጳውሎስ ምልምል ካድሬ አቡን፣ ቁልፉን ለማስረከብ እየተደራደሩ እንደሆነ እሑድ ዕለት እራሳቸው **ስብሰባ** ላይ አፍረጡት አሉ። ድርድሩም እንደተባለው አልቆ ቁልፉን እስካሁን ሳያስረክቡ አይቀሩም ብለን "ዋይ ዋይ!" እያልን ነው። ሜዳ ላይ የተበተነው መንጋው ይኸን ሰምቶ ተበጥብጧል። ከሁሉም ከሁሉም፣ የዘንድሮው ችግራችን ጫን ያለው ነው።

> **ይሻላት እንደሆን፣ ገዳም ቢወሰዷት**
> **ታማለች እያሉ፣ አባባሱባት።**

ማለት ይኸው አይደል!

## ከሥረ-መሠረቱ

የሎንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያናችን፣ ወያኔ ከገባ ጊዜ ጀምራ አንድም ጊዜ ሰላም አግኝታ አታውቅም። እንዲሁ እንደታመሰች ነው። ምዕምኑ ሲቃዩን እንዳየ ነው። ሁሌ ግን አምላካችን እንደታደጋት፣ ዛሬን ደርሰናል። የሚመጣላት እረኛ ሁሉ የጌታን መንጋ የሚበትን እንጂ የሚሰበስብ ሁኖ አልተገኘም። በተለይ ሹመት ብጤ ያላቸው፣ አቡን በሉ፣ ቆሞስ በሉ፣መነኩሴ በሉ፣ ሊቀ ካህናት በሉ፣ ... ሁሉም የጌታን በጎች የሚበትኑ የበግ ለምድ የለበሱ ተኲላዎች እንጂ የሚሰብስቡ እረኞች ሁነው አልተገኙም። ገንዘብና ሥልጣን የማይበክለው ሰው ባይኖርም፣ አሁንስ አባባሱባት!

ኮማንደር አሰፋ ሰይፉ፣ መጋቢት ፬ ቀን ፪ሺ፭ በተለያዩ ድረ-ገጾች (ኢቲዮሜዲያ፣ ኢካዲኤፍ) በጻፉት ጦማር መነሻ ምንጬን ቅልብጭ አድርገው አስቀምጠውልናል[i]። ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም (24th October 1993)፣ አሁን በቅርቡ መልአከ ሞት የገላገለን (አፈር ይክበዳቸው) የወያኔ ሹመኛ ታጋይ ፓውሎስ፣ የሎንደን ሕዝብ እንዳይመጡብን እያለ፣ ሆድ አደር፣ ሙሉጌታ አሥራተ እየመራቸው አመጣቸው። ከሰማይ በታች፣ ማንም ሊደፍረኝ የሚችል ኃይል አይኖርም ባዩ ቀኖና አፍራሹ፣ የወያኔ ፓትሪያርክ ዓይናቸውን በጨው ታጥበው ሲመጡበት፣ የሎንደን ሕዝብ ተንጫጫ። ከምንም ሳይቆጥሩት ገብተው ቀድሰው ሊወጡ ሲሞክሩ፣ በጀግኖቹ የኢትዮጵያውያ ልጆች እጅ ድብድብ ተደረገ። የ$50,000 ዶላር ሮሌክስ ሰዓታቸውን ወልቆ ወደቀባቸው። አንዱ በቦክስ ሲያቀምሳቸው፣ ቆባቸው ከራሳቸው ላይ በረረች።ቆሌያቸውም አብሮ ተገፈፈ። ደጋፊዎቻቸው "ምንስ ቢሆን፣ ጳጳስ እንዴት ይመታል!" እያሉ ተንጫጩ። ጌታ እይሱስ ቢሆን፣ የአባቱን ቤት ነጋዴዎች፣ ሌቦችና ቀማኞች ተንሠራፍተውበት ባየ ጊዜ ተናዶ፣ ጅራፍ ገምዶ እየገረፈ አልነበር ያባረራቸው! ምን አዲስ ነገር መጣ? ሌባ ተይዞ ለመሆኑ ዱላ ይጠየቃል? ሙሉጌታ አሥራተ ካሣ ባይኖር፣ ግብዐተ መሬታቸው በዚያን ዕለት በተፈጸመች ነበር። ያ ተሳክቶ ቢሆን ኑሮ፣ እስከአሁንም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ላይ ያደረሱትን ውጥንቅጥ ጥፋቶች ባልደረሱ ነበር። ዋልድባ ገዳምም ባልተደፈረ ነበር። ሮሌክሳቸውን እንኳን ከወደቀበት ሳያነሱ "ሾፌሬ አውጣኝ" ብለው ከዚያች ቦታ በርረው ጠፉ። ለመሆኑ፣ ሮሌክስ ሰዓት መነኩሴ ያስራል ብላችሁ ገምታችሁ ታውቃላችሁ! ጉድ እኮ ነው! ሎንደኖች የዚያን ጊዜ አደጋ በዚሁ ሁኔታ ተገላገሉት። አሁን ካጋጠመን አደጋ ግን አይብሰም! ያ ያኔ ነበር። ዘንድሮስ በቤተክርስትያኗ **<u>አባብሰውባታል።</u>**


THE DAILY TELEGRAPH MONDAY OCTOBER 25, 1993

Six held in Ethiopian Church row

By Tim King

A REPRESENTATIVE of the Archbishop of Canterbury was caught up in ugly scenes surrounding yesterday's morning service at the Ethiopian Orthodox Church in London where police arrested six people.

Dr Richard Marsh, the Archbishop's assistant secretary of ecumenical affairs, had gone to the church in Down Street to greet Patriarch Paulos, who arrived in Britain last Tuesday. The church is leased by the Diocese of London to the Ethiopians.

Dr Marsh was met by supporters of a faction of the Ethiopian Orthodox Church which refuses to recognise the authority of Patriarch Paulos.

When the Patriarch arrived to take the service the demonstrators tried to prevent him entering the building. He managed to enter the church only with the help of police, who could not prevent demonstrators bursting in after him.

As police tried to mediate between the factions, they asked Dr Marsh, who is a priest of the Church of England, to convey messages to the Patriarch as he stood in the inner sanctum.

The Patriarch refused to leave the church until he had finished saying the liturgy.

Dr Marsh said: "There was an awful lot of shouting and confrontation. It was very aggressive." He said on behalf of the Archbishop: "We are very distressed to see such incidents taking place in God's house."

Riot police were deployed in Savile Row to separate the warring factions.

There were five arrests and two men were charged. The others were later released.

When the Patriarch left the church after reciting the three-hour liturgy, a man smashed the side window of his car. He was arrested and then released on bail.

The Patriarch returned to Addis Ababa last night.

አቡነ ዮሐንስ (አባ አረጋዊ) ታኅሣሥ 15 ቀን 1990 (24 December 1997) አረፉ። አንድ የሕዝብ ወገን የሆኑ ቄስ (ዛሬም የሕዝብ ወገን ናቸው) እና በጊዜው የነበሩ ዲያቆናት፣ በሰላም የእግዚአብሔር በጎች ሳንበተን ሰብስበው እንደ መልካም እረኞች ሲጠብቁን ቆዩ። በቄሱ በጣም ደስተኛ ነበርን። ምንም ሌላ አባት አላስፈለገንም። ታጋይ ጳውሎስ አድብተው **ሲጠባበቁ** ኑረው በድፍረት አንድ ቀን ደስታችንን ሠረቁት።በዚያው ዓመት ዓብይ ጾም በገባ በስድስተኛው ሳምንት ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገብረአማኑዔል የተባሉ እሳት የላሱ፣ ትንታግ ካድሬ፣ የታጋዩን ፓትርያርክ ደብዳቤ እያውለበለቡ ከተፍ አሉ። "ያውላችሁ፣ ከዛሬ ጀምሮ አስተዳዳሪአችሁ እኔ ነኝ። የቤተ ክርስቲያኗን ንብረት በሙሉ አስረክቡኝ" የምትል ቀጭን ትዕዛዝ አውደ ምሕረቱ ላይ አስነበቡልን። "ሆሆሆይ! የማነው ቀብራራ! ለጌታው ያልተበገረን ለአሽከሩ እነበገር መሰለው"? በጊዜው የነበሩ የሰበካ ጉባኤ አባላት፣ ጊዚያዊ አስተዳዳሪውን ጨምሮ፣ እንደዛሬው ሳይሆን ቆራጥ የሕዝብ፣ ወገን ነበሩና "ጊዜው የንሰሐ ጊዜ በመሆኑ አሁን ስለንብረት መነጋገር አንችልም" ብለው ነገሩን ዘጉት። ሰውዬው የተላኩበትን ጉዳይ ሳይፈጽሙ በመቆየታቸው አንጀታቸው አረረ። ከሁለት ሳምንት በኋላ ሕዝቡ ለትንሳኤ በዓል ቤተክርስቲያን አድሮ ስምንት ሰዓት ገደማ ወደ ቤቱ ለመሄድ ሲዘጋጅ፣ ካድሬው አምባገነን፣ መነጋገሪያን (ማይክሮፎኑን) ከአንድ ዲያቆን እጅ ነጥቀው በንዴት፣ በዕቢትና እና በንቀት ሕዝቡን ዘለፉት! ምዕምኑ ተንጫጫ። አሁንም አደጋው የታያቸው የሰበካ ጉባዔ አባላት፣ ነገሩን አብርደው ወደየቤታችን በሰላም እንድንሄድ አሰናበቱን።

ሳምንቱን በየቤታችን በጥሩ ሁኔታ አሳልፈን ለዳግማዊ ትንሳኤ ቤተክርስቲያን ስንሄድ ልክ አሁን እንድተፈጸመብን በደል ፣ ታሽጋብን ጠበቀችን። ታሪክ ሲደገም አያችሁ! ተረበሽን! ማን ዘጋብን ብለን ተጯጯህን። ሊቀ ካህናት ብርሀኑ ገብረአማኑዔል፣ ሙሉጌታ አሥራት፣ እና ሊቀ-ሊቃውንቱን ጨምሮ ሌሎች የወያኔ አሽከሮችና ከቤተክርስቲያኗ የተባረሩ የታጋይ ጳውሎስ ደጋፊዎች እንደሆኑ ደረስንበት። እኒያ ከሕዝብ ወገን የነበሩ አባትም ከኛው ጋር ስለነበሩ፣ የዝናብ ዶፍ እየወረደብን፣ ግሪን ፓርክ ቁመን የዳግማዊ ትንሳኤን ጸሎት አደረስን። መኖር ደግ ነው። ዛሬም እሳቸው ናቸው ከኛ ጋር የቀሩት። ከዚያች ሰዓት ጀምሮ፣ የሰበካ ጉባኤ አባላት ተሯሩጠው፣ በሕጋዊ መንገድ ቤተክርስቲያናችንን ሲያስከፍቱ፣ ካድሬው ካህንም በመጡባት አኳኋን አፍረው ወደ መጡበት ተመለሱ። ምስጋና ለእግዚአብሔር! የያኔውን በአምላክ ቸርነት በቀላሉ ተገላግልን። ያሁኑ ግን ይብሳል። አድፍጠው የሕዝብን አመኔታ ያገኙት "መነኩሴ" ቁስሏን የባሰ አቁስለው ሕመሟን **<u>አባባሱባት</u>**።

አንዱን ችግር ስንወጣ፣ ተኝቶ የማያድረው ሰይጣን ሌላ ችግር ይጋርጥብናል። በታጋይ ጳዉሎስ ንዝነዛ የግሪን ፓርኩን ቤተክርስቲያን ለቀን እንድንወጣ አንግሊካን ቤተክርስቲያን ወሰነብን። ታቦት ይዘን ቤት አልባ ልንሆን ምንም አልቀረንም ነበር። እንዲያም ሁኖ ችግሩ ግን ከአሁኑ አልባሰም። አሁን አድናንታለሁ እያሉ **<u>አባባሱ</u>**ባት! የያኔ ታሪኩ ብዙ ነው። ማወቅ የፈለገ፣ በስተግርጌ ያለው ማጣቀሻ አንብቦ መረዳት ይችላል"። ችግሩን **ለጊዜው** ፈታነው። አዲስ ቤተክርስቲያንም ባተርሲ ተከራይተን ገባን።

# <u>የሎንደኑ ራስፑቲን</u>

የራስፑቲንን ታርክ በአጭሩ ጽፌ ባለፈው ሰሞን፣ በኢትዮሜዲያ፣ በኢኤምፍ፣ በኢካዲኤፍ አስነብቤአችሁ ነበር። ብዞዎቻችሁ አንብባችሁ ገንቢ ሀሳብ ሰጥታችሁኛል አመሰግናለሁ። ያንን ያነበቡ የሎንደን ወንድሞቼ፣ ምነው ስለለንደኑ ራስፑቲን አትጽፍም ብለው ወተወቱኝ። የሎንደኑ ራስፑቲን ታርክ እንደ ራሺያዊው ታሪክ ባይጥምም፣ እንግዲህ የአንባቢዎቼን ጥያቄ ማሟልት ስላለብኝ፣ እንዲሚከተለው እጽፋለሁ። (የራሻውን ራስፑቲን ታሪክ ያላነበበ ካለ፣ በኢትዮሜዲያ ላይ እስከ በፊት ገጽ ዛሬም ስላለ ማንበብ ትችላላችሁ http://www.ethiomedia.com/addis/rasputin_the_menacing_monk.pdf )

ትንሽ ከዚያ ከነበረብን ግርግር ቀደም ብሎ ሌላም **የታጋይ** ጳውሎስን ደበድቤ ይዘው መጡ የሚባሉ ጎረምሳ "አባት" አሉና ተጠንቀቁ ተባልን። በዓይነ ቁራኛ እንከታተላቸው ገባን። እንዲያው ለነገሩ ነው እንጂ፣ ታጋይ ጳውሎስ ካልላኳቸው እንዴት ይመጣሉ? የመንግሥት ዲፕሎማት አያደሉ። በእስኮላርሽፕም አልመጡ። በቦሌ እንጂ በባሌ አልወጡ። በሆነ መንገድ ብቻ መጥተዋል። ምስጢሩ ተከድኖ ይብሰል። እሳቸውም፣ ካድሬው ሊቀካህናት ብሩሀኑ ገብረአማኑዔል ላይ የደረሰባቸውን ውርደት ዓይተውም ይሁን በሌላ ምክኒያት የታውቀ ነገር የለም፣ ብቻ አለኝ ያሏትን ደብዳቤአቸውን ደበቁና (እስከዛሬም አላሳዩም) ስማቸውን ከግሩም ወደ ግርማ ቀይረው፣ "አባ" ተብለው ቤተክርስቲያኑ መድብ ላይ ተመቻቹ። ካህናት፣ ዲያቆናት እና ከምዕምኑም አንድ በአንድ በፍቅር ውድቅ ይልላቸው ጀምር። መስተፋቅር አላቸው መሰለኝ። መሠረታቸውን ጣሉ። ልክ **እንደ ራስፑቲን** ሰውን (በተለይ ሴቶችን) የመማረክ ተሰጥዖ ስለነበራቸው፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ አንገታቸውን ሊሰውላቸው የተሰጋጁ ወዳጅ ሴቶችና ብዙም ያልበሰሉ ወጣት ተከታዮች አፈሩ። ጥቂት በዕድሜ ከገፋነው በስተቀር (እኛም ኋላ ላይ እጅ ሰጠን)፣ እኚህን "አባት" የሚከተሉ ጎረምሶችና ኮረዶች እየበዙ መጡ። ብቻ ምን ያደርጋል፣ "ዳግማዊ ራስፑቲን" ማለቱ ይቀላል። እንዲህ እንዲህ እያሉም ሥር ሰድደው፣ እኒያን <u>የሕዝብ ወገን የሆኑትን ትሑት ካህን</u> መፈንቅለ መንበር (ኩ ዴታ በሉት) አካሂደው የአስተዳዳሪነቱን ቦታ ለመያዝ የተለያዩ ሸሮችን መሸረብ ጀመሩ። ነገሩ የጥቅምና የሥልጣን ጉዳይ ስለሆነ ብዙም አላስጨነቀንም። እንዳሁኑ ግን የቤተክርስቲያኗን ሥቃይ **<u>አላባባሱባትም</u>**። መንኩሴ ናቸው ይባላል። አንድ ሰው ሲመነኩስ እንደ ሞተ ሰው ይገነዛል ሲሉ እሰማለሁ። ከዚያ በኋላ ያ ሰው ሙቷልና በፍጹም ለሥጋው አይሳሳም። ሕይወቱን ሙሉ እግዚአብሔርን ሲያገልግል ይኖርና ወደአምላኩ በሰላም ይሰበሰባል ሲባል እሰማ ነበር። ከታጋዩ ከፓትሪይርክ ጀምሮ እስከ የሎንዶኑ ራስፑቲን ድረስ ለሥጋቸው ሲሉ፣ ሲገድሉና ሲያስገድሉ ነው **የማየው እንጂ ሙተው አላየኋቸውም**። እንዴት ነው ነገሩ! አባባሉ ተረት-ተረት ይሆን?

# አድመኛው አባ

ሀ ሲል ገና ሲጀመር፣ አባ ራስፑቲን (ከዚህ በኋላ "አባ" ብዬ ነው የምጠራቸው - ክብራቸውን ላለመቀነስ፣ "አቶም" "ታጋይም" አልላቸውም) ሲጫወቱ መቸም አፍ ነው የሚያስከፍቱት። ተከለ ሰውነታቸው፣ ቁመናና፣ ዛላቸው ለዚህ ዓለም ተለክቶ እንጂ ለገዳም የተሠሩ አይመስሉም። አንዲት ጥንቅሽ የመሰለች ልጅ አግብተው ቢሆን ኑሮ፣ ደህና ብረት መዝጊያ የሚሆን አማች ይወጣቸው ነበር። እንዲያው ወደ ሎንደን ገዳም በዚህ ለጋ ዕድሜአቸው ምን አስመነናቸው! አንዳንዴ ያሳዙኑኛል።

አባ፣ በጥቂት ጊዜ ውስጥ፣ ወጣት መዘምራን ወንዶችንና ሴቶችን በቀላሉ በቁጥጥራቸው ውስጥ አዋሉ። ቀጥለዉም ወሳኝ ሚና የነበራቸው ሰበካ ጉባዔው ውስጥ የነበሩ ወጣት ዲያቆናት አሳምኑና አሳምጹ። እንደሚመስለኝ ከሆነ፣ የወጣቱን ቋንቋ መናገር ስለሚችሉ በቀላሉ ወደ እነዚህ ልብ ገብተው ለመንሰራፋት መንገዱ ቀና የሆነላቸው ይመስላል። ሰበካ ጉባኤ ዉስጥ የገንዘብ ሃላፊ የነበሩት ሰዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ቁጥጥራቸው ሥር አዋሉ። <u>ለጊዜያዊው አስተዳዳሪው</u> ይከፈል የነበረውን አበል ለብዙ ወራት አስቀርተውባቸው ካህኑና ቤተሰባቸውን በበለጸገ አገር እየኖሩ ለረሀብና ለችጋር የተጋለጡበት ሁኔታ ፈጠሩባቸው። ነገሩን ቶሎ አይተን ውሳኔ እንድንሰጥ ከተመደቡት ምዕምናን መሀል፣ እኔም በግድ ተምርጬ ገብቼ ነበር። አንድ ቀን ጠቅላላ ጉባዔ ጠርተን ሶስት ሰዎች ስብሰባውን ስንመራ፣ አባና ዲያቆናት ተከታዮቻቸው ሕዝቡን እየሰደቡ አስቸገሩን። በለሆሳስ ድምጽ፣ "ደንቆሮ ሁሉ! ምንም እኮ የቤተክርስቲያን ሥርዓት አያውቁም። መሀይም!" እያሉ ሲሳደቡ፣ ሰምቼ ትዕግስቴ አልቆ "ሕዝብን አይስደቡ። ሕዝብን ያክብሩ! ሕዝብን አይናቁ" ብዬ እንደጮኹኩባቸው ትዝ ይለኛል። እንዲያው እዚህ ላይ አንድ ነገር ልበል። ለመሆኑ፣ ለነዚህ ሊቀ-ሊቃውንት መሀይም መንግሥተ ሰማያት አይገባም ብሎ ያስተማራቸው ማነው? ከይሁዳ በስተቀር፣ ከ12 ሁለቱ ደቀመዛሙርት፣ የትኛው ነበር ሊቅ? የተናቀ ሥራ ይሠሩ የነበሩና ዓሳ አስጋሪዎችም አልንበሩም? ሊቀ-ሊቃውንትማ አስሰቀሉት! ሐዋሪያው ጳውሎስ በመጀምሪያው መልዕክቱ ወደቆሮንቶስ ሰዎች (ም13 ቁ1-2) ስለሊቅነት እንዲህ ይላል!

> ***"በሰዎችና በመላአክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሸዋ ጽናጽል ሁኜአለሁ። ትንቢትም ቢኖረኝ፣ ምሥጢርንም ሁሉን ዕውቀትን ሁሉ ባውቅ፣ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ቢኖረኝ፣ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ"***

ሊቃናት ተብዬዎች የዋሁን ቄስ፣ ብዙ የቤተክርስቲያን ዕውቀት እንደሌላቸው ነበር የሚከሷቸው! ታዲያ እኒያ <u>ከሕዝብ ወገን የነበሩቱ አባት፣</u> "ከሊቃውንቱ" (ድንቄም እቴ!) የሚሰነዘረው ስድቡ በዝቶባቸው ቤተክርስቲያኗን ጥለው ሊወጡ ወደ በር ሲሮጡ፣ ሁኔታውን ዓይተው የደነገጡ ሰዎች ተማጥነው ሊመልሱ ሲከተሏቸው፣ "አድማ አስመቺው"አባ፣ በሚያስደንግጥ የአራዳ አባባል፣ "ተወው! ጥርግ ይበል!" ሲሉ ጆሮዬ ጥልቅ አለ። ማመን አቃተኝ። በጣም አዘንኩ! አትናገራቸው፣ "ካህን" ናቸው! ያውም መነኩሴ! አትተዋቸው፣ ዓለማዊው ሰው እንኳን በግልጽ ለማለት የማይደፍረውን ባልተገራ አንደበት ሲናገሩ ትሰማቸዋለህ! ለመሆኑ ዕውነተኛ መነኩሴ ናቸው ወይስ አክሴማ የለበሱ አስመሳይ የቀበሮ ባሕታዊ?!

በሕዝብ የተመረጠው ኮሚቴ፣ እኒያ <u>ምስኪን ቄስ</u> ተበድለዋለና የሠሩበት ገንዘብ ይከፈላቸው ብለን ወሰንን። ውሳኔውን ማን ሥራ ላይ ያውለው! ማን ሊተገብረው! የአባ ተከታዮች አላገጡብን። በዚህ ላይ በስም ማጥፋት ዘመቻ ቀጠሉ። ወረቀት እየጻፉ በየሳምንቱ የቤተክርስቲያኗን ግቢ አጥለቀለቁ። ካህናት ሲበጣበጡ ሳይ የመጀመሪያ ጊዜዬ በመሆኑ በጣም ገረመኝ። ለካስ ከኛ በማናቸውም አይሻሉም። <u>ምስኪኑ ቄስ፣</u> ስቃዩ በዝቶባቸው፣ ቤታቸውን፣ ባለቤታቸውን፣ ወርቅ-ወርቅ የመሰሉ ልጆቻቸውን ትተው አገር ጥለው ወደ አሜሪካ ተሰደዱ። አሳዳጆቻቸው በደስታ ቧረቁ! እኛም <u>"ምን አገባን"</u> ብለን አስጠቃናቸው።

ቄሱን ካባረሩ በኋላ፣ የኛው አባና አድመኞቹ ተንሰራፍተው ተቀመጡ። እኛም ቤተክርስቲያኗ ለወያኔ እስካልተሰጠች፣ ይኸ የሥልጣንና የገንዘብ ጉድይ ነውና እንደፈለጉ ይሁኑ ብለን ችላ አልናቸው። ግራም ነፈሰ ቀኝ፣ ዋናው ነገር፣ አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የሚያሰባስበን ጃንጥላ መኖሩ ጥሩ ነው ብለን ታገስን። አንዳንድ ሥርዓቶችንም ቀየሩብን! ከሁሉ ከሁሉ ያበሸቀኝ የነበረው፣ ሥጋ ወደሙ ሲሰጥ፣ "እስመ ኃያል አንተ፣ እኵት ወስቡዕ፣ ወለከ ስብሀት ለዓለመ ዓለም" እያልን በጥልቅ ንሰሐ እግዚአብሔርን በዚያች ሰዓት እንኳን እንዳናመሰግን ሥርዐቱን ለውጠውብን፣ አብዛኛውን ጊዜ እንጨት-እንጨት በሚለው የስድብ ትምህርታቸው ተኩት። እኛ በሀይማኖቱ ሥራዐት "መሀይም" በመሆናችን፣ በየትኛው አፍ "እንዳይረብሹን" ብለን አንናገራቸው ነገር!! አባማ ማይክሮፉን ከያዙ፣ አለቀልን። ጆሌአቸው ያልሆነው ግለሰቦች ሥጋ ወደሙን ልንቀበል ከተሰለፍን በአሽሙር ይገሽልጡናል። አንዳንዶቻችን ላለመሰናከል፣ ሰውዬው በዚያች ሰዓት ሰበካ ከጀመሩ፣ ሥጋ-ወደሙን መቀበል ከነአካቴው ተውነው። በዚህ ሁኔታ ሁሉንም ችለን ኖርን። አባም የአሸናፊነት ስሜት ተሰምቶአቸው ተዝናኑ። ከኋላ የመጣ ዓይን አወጣ ይባል የለ? ምን ድግምት አዞሩብን?

በእንዲህ ሁኔታ እያለን፣ እኒያ <u>አገር ጥለው የጠፉት ቄስ</u> ነገሩ በረድረድ ሲልላቸው፣ አባም በአሸናፊነት ከተደላደሉ በኋላ፣ ከአንድ ዓመት በላይ ተሰደው፣ የባለቤታችውና ልጆቻቸው ናፍቆት ጠንቶባቸው ነው መሰልኝ "የሆነው ይሁን" ብለው ተመልሰው መጡ። ስደተኛው ቄስ፣ ከሄዱበት ከተመለሱ በኋላ፣ የተንሰራፉትን የአባን ስልጣን ትተውላቸው፣ ለራሳቸው ዩኒቨርሲቲ ገብተው በቢኤ ተመርቀው፣ ሁለት መጽሐፍ ጽፈው ለንባቢ አብቀተው፣ ማስተርሳቸውን ቀጠሉ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን አንድ ጥሩ አጋጣሚ ለቤተክርስቲያናችን መጣ። ይኸውም፣ የተከራየናትን የቤተክርስቲያኗን ሕንጻ እንድንገዛ፣ ባለቤቶቹ መከሩን። አተካሮው ሁሉ ቆመና፣ ሁሉም ቤተክርስቲያኗን ለመግዛት መሯሯጥ ተጀመረ። አባም እዚህ ላይ ሊረሳ የማይቻል ወሳኝ አዎንታዊ  ሚና መጫውት ጀመሩ። ያን አድመኛ ጳባያቸውን በጉያቸው ወሸቀው፣ ትንሹንም ትልቁንም "አንቱ!" እያሉ፣ ሁሉም ገንዘብ ማዋጣቱ ላይ እንዲረባረብ፣ **እግዚአብሔር** የሰጣቸውን የማግባባት ችሎታቸውን ለደግ ነገር አዋሉት። ፍቅር አሳዩን! እሳቸውም በሚገርም አኳኋን የተለወጡ መሰሉ። የታመመን ጠያቂ፣  ለተቸገረ አዛኝ፣ ለተበደለ ተቆርቋሪ ሆነው ተገኙ። ሰላም ተገኘ። ፍቅር ታሸንፋለች ይባል የለ? በቃ አባ አውራ ሆኑ። ሰይጣን ፍቅር ቢያሳየን እንወደው ይሆን? እኛ እኮ ሞኞች ነን። ከአባ በኋላ ፈራሁት! አድነነ፣ ከመዓቱ ሰውረነ!

# ምርኮኞች!

ሁለተኛውን የቅዱስ ፓውሎስ መልዕክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ምዕራፍ ፲፩ ቁጥር ፲፬ አንብቤ በጣም ገረመኝ። እንዲህ ይላል። **"ይኸ ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ፣ የብርሀንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና።"** ወቸ ጉድ! ለዚህ ኑሯል ለካ ከኔ ጀምሮ የኃጢአተኛው ቁጥር እንዲህ እንደ አሸዋ የሚበዛው!


የአገራችን፣ የኢትዮጵያ ምርጫ ፺፯ ሰባት መጣ። ወያኔ ወገናችንን ኢትዮጵያውያንን በጠራራ ጸሐይ ጨፈጨፈ። ከዚህ በፊት፣ (የቀሲስ አስተራዬን ቃል ልዋስና[iii]) አንድ ሁሌ የሚከዱን ሊቀ-ሊቃውንት "ደፍተራ" (ሆድ አደር ሙሉጌታ አሥራተ ካሳ ቤተክርሲቲያን ሲያዘጋብን እሳቸውም ተባባሪ ነበሩ) "ፖሊቲካና ሀይማኖት አብረው" አይሄዱም እያሉ፣ "ወያኔን የምትቃወሙ ቤትክርስቲያኗን ጥላችሁ ሂዱ" እስከማለት ደርሰው ስለነበረ፣ አንድም ቄስ አገራችን ውስጥ ለሚፈጸመው ጭፍጨፋ በግልጽ መቃወሙ የማይታሰብ ነበር። አባ ያንን ግድግዳ፣ በምርጫ ፺፯ ወቅት ደረመሱት። ሎንደን ቤተክርስቲያን ውስጥ፣ የሕዝብ ወገንነታቸውን ያለማወላውል አውደ ምሕረቱ ላይ አወጁ! የተደረገውን ጭፍጨፋ አወግዙ! ምን???? ብዙዎቻችን ልባችን ተተርትሮ **ተፈታላችሁ**። "እንዲህ ነው እንጂ አባት!" አልን። ከዚያም አልፈው ተርፈው፣ ከዚያ በፊት የማይታሰበውን፣ አባ፣ ሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በድፍረት ሰተት ብለው መጥተው ተቀላቀሉን! እኔ ከዚያ በፊት ስሸሻቸው የኖርኩት ሀጢያተኛ፣ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ሳያቸው፣ ተንደርድሬ ሂጄ ነበር እግራቸው ሥር ተነጥፌ መስቀላቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳለምኩት! እጄን ሰጠሁ። ተማረኩላቸው። ሌሎችም እንዲሁ! አሁንም ፍቅር ያሸንፋሉ ያሉት ይኸን ነበር ልካ! ከዚያ ወዲያማ ተውት! አባን የሚያክል ካህን ከየት ሊመጣ! የሳቸውን ክፉ ነገር የሚያነሳብኝን ሁሉ የማርያም ጠላት ነበር አድርጌ የማየው። ቤተክርስቲያኗም ጭፍጨፋውን በግልጽ አወገዘች። እሳቸውን ተከትለው፣ አንዳንድ ካህናትም ሰልፍ ላይ መገኘት ጀምሩ።እልልል!

የቤተክርስቲያኒቷ አስተዳዳሪ ምርጫ በፈረንጆቹ አቆጣጠር 2006 ላይ ደረሰ። አንድ እጃችንን ሳይሆን ሁለቱንም አውጥተን፣(ነውር ባይሆን እግሮቻችንንም በጨምርን) አባን መረጥን። በሕዝብ ይሁንታ፣ የቤተክርስቲያኗ አስተዳዳሪ ሆኑ። ትዝ ይለኛል፣ አንድ **ወንድማችን፣** የሰበካ ጉባኤው ምክትል ሊቀ መንበር፣ የአባ የብዙ ጊዜ ወዳጅ፣ እሳቸው ሲመረጡ፣ እንዲህ ነበር ያላቸው። "ቤተክርስቲያኑን እንዲያስተዳድሩ፣ **<u>በዲሞክራሲ</u>** (እኛ ሳናውቀው "በቴዎክራሲ" ይሆን የተመረጡት?) የመረጠዎት ይኸ ምዕምን ነው። እዚህ ቦታ የሚቅመጡት፣ ለሶስት ዓመት ብቻ ነው። ከሶስት ዓመት በኋላ፣ ሌላ ምርጫ ይደረጋል። ሕዝቡ ከፈለገዎት እንደገና ይመርጥዎታል። ይኸ ምዕምን እስከፈለገዎት ብቻ ነው ሥልጣን ላይ የሚቆዩት። መውረድ ሲገባዎት በሰላም ይወርዳሉ። እስከዚያው ግን ደብራችንን ያስተዳድሩልናል።"  ያስታውሰው ይሆን? ዳሩ ምን ያደርጋል! ነበር ሁኖ ቀረ እንጂ! ለማንኛውም አባ ከተመረጡ በኋል ጥሩ ጥሩ ሥራዎችን አከናውነዋል። ቤተክርስቲያኗ እንደትገዛ ብዙ ጣሩ። አስተባበሩ። እኛም ገንዘባችንን ዘረገፍን። ሴቷ የወርቅ ሀብሏን አውጥታ፣ የጆሮ ጌጧን አውልቃ ለቤተክርስቲያን አስረከበች። ደመውዝተኞቹ፣ በየዓመቱ አንዳንድ ሺ ፖወንድ ለመስጠት ቃል ገብተን፣ ገፈገፍናት። ከሁሉ ከሁሉ የሚያሳዝነው፣ ሴቶች በየሳምንቱ፣ እንጀራ ጋግረው፣ ወጥ ወጥውጠው ያመጡና ለቤተክርስቲያን መግዣ ተብሎ በብርድ እየተንቀጠቀጡ ቁመው ይሸጡ ነበር። ምን እሱ ብቻ! ያመጡትን እንጀራ ሲርባቸው አይበሉም። ገንዘባቸውን አውጥተው የሠሩትን ምግብ ገዝተው ነበር የሚመገቡት። ዕውነቴን ነው!

ሎንደን ውስጥ የነበሩ አርቲስቶች በነቂስ ወጥተው ተአምር ሠሩ። "ያንተን ላንተ" የሚል መንፈሳዊ የመዝሙርና የድራማ ፕሮግራም ሠርተው ሕዝቡን ቀስቀሰው ብዙ ሺ ብር አስገኙ። **ያ ሲዲ/ዲቪዲ** ከሎንደን አልፎ፣ አሜሪካን አገር እያንዳንዱ ክርስቲያን ቤት ገብቶ እስከዛሬ **ይባርካል።**

የአባ ዝነኛነት፣ ለአንዳንድ ካህናት አልተዋጠላቸውም። የሕዝብ ወገንተኛነታቸውንና፣ በጣም ተወዳጅ (popular) እየሆኑ መምጣታቸውን ያዩ፣ ጨርሶ ማንም ካህን ከነሱ ቁጥጥር ውጪ እንዲሆን የማይፈልጉት፣ በፊት ከሳቸው ጋር አድመው ለአስተዳዳሪነት ያበቋቸው አንዳንድ ካኅናት፣ አባን በነገር መነኋታተል ጀመሩ። አባ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሕዝቡ መሀል ሥር በመስደዳቸው እሳቸውን ነክቶ ማን በሰላም ሊኖር! ያ መሀይም ብለውት የነበረው ሕዝብ ይከላከልላቸው ገባ። ዕውነትም መሐይሞች ነን። የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በትራፋልጋር ስኩዌር ሲከበር፣ አባ ቤተክርስቲያኗን ከጎናችን አሰለፏት። በዚያ ምክንያት ከካህናት ተቀናቃኞቻቸው የተሰነዘረባቸውንም ጥቃት ሕዝብ ግድግዳ ሁኖላቸው ተከላከለላቸው። አባ ሕዝቡን ይዘው ተቃዋሚዎቻቸውን ድባቅ መቱ። ይገርማል፣ አንዴ ካህናቱን ይዘው ይወቁናል፣ ሌላ ጊዜ እኛን ይዘው ያደበዩአቸዋል። እንደ አባ ሰው ተጥቅሞ እንደማስቲካ የሚተፋ፣ ወያኔን ብቻ ነው ያዩት። ቤተክርስቲያኗን የመግዛት አቅማችንም እያደር ዕውን ሆነ።

**በ2005 ኢ.ም.** ቤተክርስቲያኗ እጃችን ልትገባ ወራት እንደቀሯት፣ ሻጮቹም ረድተውን፣ የምንገዛበትን መንገድ ሲያመቻቹልን፣ የውስጥ ቦርባሪዎች ዜናውን አዲስ አበባ አደረሱት። የአዲስ አበባው ታጋዩ የወያኔ ፓትሪያርክ አንድ የሚያሳፍር ነገር ሠሩ። እንደምንም የሻጮቹን አድራሻ ቆፍረው አግኝተው፣ “እኔ የማላውቃቸው፣ ከኔ ትዕዛዝ ውጭ ያፈነገጡ ክርስቲያን ያልሆኑ አረመኔዎች ናቸውና፣ ለነሱ እንጻውን እንዳትሸጡት” የሚል ቀጭን ትዕዛዝ ያዘለች ደብዳቤ ጻፉላቸው። ድብዳቤዋም ይኸቻት!



-2005 13:22 FROM:SOUTHWARK DIOCESE 02079399468 TO:972424327 P:2/2
/05 2005 16:01 FAX 251 1 552211 EOC-PRIVATE-SECRETARY 001

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት
Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Patriarchate Private Secretariate

Ref. No 015/640/97

Rt. Rev. Thomas Butler
Bishop of South wark
London
Fax 0044 2087694126

Our greetings in the name of Our Lord and Savior Jesus Christ.

It is with a great sense of gratitude that we have taken note of the fact that your Diocese is currently in discussion with the Parish Council of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church of St. Mary of Tsion, with regard to the sale of St. Phillip's Church Queenstown Road, Battersea, London.

We would like to avail ourselves of this opportunity and remind you that any agreement that does not involve the active participation of His Grace Abune Yosef, EOTC's Arch-Bishop to Europe would not be regarded as valid by our Church's Supreme authority, The Holy Synod.

We, therefore, suggest that your office gets in touch with the above mentioned legal representative as soon as possible.

The Address of His Grace Abune Yoseph is:

His Grace Abune Yoseph
Archbishop of EOTC for all Europe
Piazza St. Petros Via 4/A
00184 Roma – Italia

Peace in Christ

Aba Serima (Dr.)

C.C
- Ecumenical office of the Bishop of Canterbury Fax 00442074019886
- His Grace Abba Yoseph Archbishop of EOTC for all Europe Piazza St. Petros Via 4/A 00184 Roma - Italia

Addis Ababa

ደግሞ አያፍሩም “peace in Christ” ብለው ይፈርማሉ። ለመሆኑ የሰላምን ትርጉም ያውቁት ነበር? ከዚህ በኋላ፣ እንደገና አባ አንድ ጀግንነት ፈጸሙ። ካህናትን አሰተባብረው ከዚያች ደቂቃ በኋላ፣ የአባ ፓውሎስን ስም ቤተክርስቲያኗ “ብጹዕ ወቅዱስ” ብላ ላትጠራ አስወሰኑ! በአድራጎታቸው ተደስተን ተንጫጫን። የፊት ጉዳችንን መች አውቀን!

አባና ካኅናቱ ይኸን ሲያደርጉ፣ አንድ የታጋይ ጳውሎስ ወገን የሆኑ አባ ሙሴ የተባሉ አቡን፣ አባ ጳውሎስን አውግዘው፣ ጥገኝነት ጠይቀው ድምጽ አጥፍተው፣ አድፍጠው አመቺ ቀን እየጠበቁ እመሀከላችን ይኖሩ ነበር። ለካስ አባ ጳውሎስን ያወገዙት፣ በጥገኝነት ሰበብ ነጻ ሕክምና ለማግኘት ኑሮ “የታጋይ ጳውሎስ ስም አይጠራም” ተብሎ ሲወሰን፣ “እንዴት ተደርጎ፣ ቡራ ከረዩ! ፋሲካ ነጩ!” ብለው ደነፉብን። ውሳኔውን ያነበበውንም ወጣት ቄስ “አውግዤሀለሁ” ብለው ዓይናቸውን አጉረጠረጡበት። ሕዝቡ ግን ጮኸባቸው። በዚህ ጊዜ ቤተክርስቲያኗ ተከፋፍላ አደጋ ላይ ልትወድቅ ምንም አልቀራትም ነበር። አደገኛ ቢሆንም፣ ከአሁን የባሰ አልነበረም። አሁን ነው ሰውዬው ሕዝቡ ዞረው <u>**ያባባሱባት!**</u> የያኔው ችግር በቀላሉ ተፈታ። ያኮረፉት ወጋኖች አባ ሙሴን ተከትለው ሌላ ቤተክርስቲያን፣ “ሥላሴ” ብለው መሠረቱ። ሥላሴም ለሁለት ተከፍሎ፣ ስላሴና ገብርኤል ተባሉ። የራሳቸው ጉዳይ!

ሰበካ ጉባዔው ከተመረጠ ሶስት ዓመት ቢያልፈውም፣ የቤተክርስቲያኗ ግዢ ስላልተጠናቀቀ፣ ሕዝቡ፣ የቤተክርስቲያኗ ግዢ እስኪጠናቀቅና **የተጀመረው መተዳደሪያ ደንብና የአደራ ሰነድ (ትረስት ዲድ - Trust Deed) የማሻሻል ሥራ ተጠናቆ በአባላት አስከሚፀድቅ ድረስ** ሰበካ ጉባዔው እንዳለ እንዲቀጥል፣ ወሰነ። እግዚአብሔር ረድቶን **የቤትክርስቲያኗ ሙሉ እዳ ተከፈለ።** በማን እጅ በአደራነት ትቀምጥ የሚለው ጥያቄ ሲመጣ፣ **ሰበካ አስተዳደር ጉባኤው፤ እንደበፊቱ እንዲቀጥል፤ አባላትን ሳያማክር ወሰነ!**

**እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2007 ዓ.ም. ቤተ ክርስቲያናችን፤ ስትገዛ፤ የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር ጉባኤ አባላት በሙሉ በሻኹዉ ላይ ቢፈርሙም ንብረቱን፤ በእንግሊዝ አገር ሕግ መሠረት፤ በግል ሰማቸው፤ ሕጋዊ ባላቤት በመሆን በአደራነት መያዝ የሚችሉት አራት ግለሰቦች ብቻ ነበሩ። ቤተክርስቲያኗ እንደትገዛ በሙያቸውና በአርቆ አስተዋይነታቸው በዘዴ ዕውን ያስደርጉ ወንድሞች (ዛሬ አባ በስልጣናችው አባረዋቸዋል) በጣም ኀበዞች ስለነበሩ፣ ሁለት ካህን እና ሁለት የሕዝብ ተወካዮች እጅ የቤተክርስቲያኗ ንብረት በአደራ ይቀመጥ በሚል ሀሳብ ነገሩ በዚያ ተፈጸመ። ፈላጭ ቆራጩ አባ እኔ አንዱ መሆን አለብኝ ብለው ቁልፏን ያዟት።**

**አባ** በደንብ አብዛኞቻችንን በዲፕሎማሲ ከያዙን ብኋላ፣ ኢየሩሳሌም ሂደው በቆረጣ፣ **የቆሞስነትን** ማዕረግ፣ ከደብሮች አስተዳዳሪ፣ ከአሁኑ ፓትሪርክ፣ ከአባ ማቲያስ እጅ፣ ተቀብለው ተመለሱ። “ይደልዎ” አልን። “ቆሙስ” ከጳጳስነት አንድ እርከን ወረድ ብሎ ያለ ማዕረግ ነው። አባ፣ ሁኔታቸው ገና ያልተሠበሩ ጎረምሳ ቢሆኑም፣ ዕድሜአቸውም ሆነ ግንፍልተኛነታቸው (unpredictable) ባሳዩት ጀግንነት አድንቀን ዝም አልን። በተፈጥሮአችን የዋሆች አይደለንም? ሰሎሞን ተካልኝ፣ “ወይ ያኔ! ወይ ያኔ፣ አንተን አያርገኝ የዚያን ቀን መጥኔ” ሲለን፣ በጫንቃችን ልንሸከመው ምን ቀረን? ልደቱ አያሌውንስ ቢሆን፣ አንድ ሰሞን ጻረ ወያኔ ሁኖ እንደትንታግ ሲንጣጣ፣ ዕውነተኛ መሪ መስሎን፣ “ማንዴላ!” ብለን አውራችን አደርገነው አልነበር? ጉድ እና ጅራት ከወደኋላ ነው እንዲሉ፣ ከተኛንበት የምንነቃው ከተበላን በኋላ መሆኑ አንዳንዴ ያናድደኛል። አባ በዚያ ሳይወሰኑ፣ አንድ አፍቃሪ ወያኔ አቡንም በቀጥታ ዘው ብለው፣ የታጋይ ጳውሎስ ስም የማይጠራበት ማርያም ቤትክርስትያን መጥተው፣ “መልአክ ጽዩን” ብለው ሾሟቸው። “**ሊቀ-ሊቃውንቱንም” ደፍተራ** “ሊቀ-ጠበብት” አሏቸው። አሁንም “ይሁን” ብለን ዝም አልን። ማን ደፍሮ አባን ሊቃወም!

በፊት፣ ከአባ ጋር ሁነው የተሳካለት መፈንቅለ መንበር ያደረጉት የተወሰኑ ዲያቆናት፣ አባ ላይ አመጹ። ለሥልጣን እንዳበቋቸው ሁሉ፣ በዚያው መንገድ ሊያወርዷቸው ሸራቸውን ሸረቡ። ወይ ካህናት! ምነው ባላውቃችሁ! በአንድ ዲያቆን መሪነት፣ ጎራ ለዩና የአባን ምትክ **ማፈላለግ ጀመሩ።** ሕዝቡን ከመጤፍ አለመቁጠራቸው ገብቶን፣ “ተዉ” ብንላቸው አሁንም እንደበፊቱ “አሻፈረን! እናንተ ምን ታውቃላችሁ! አንሰማችሁም” አሉን። ሁለት ስሕተቶች ሠሩ። አንዱ ስሕተት፣ አባን ለመገልበጥ በዋናኛው ሲታገል የነበረ ሊቀ ዲያቆን፣ አዲስ አበባ ሂዶ ከታግይ ጳውሎስ ጋር የተነሳው ፎቶና ቪዲዮ መገኙቱ ነበር። እሱም አባ እጅ መግባቱ! ያም ባልጨነቀን ነበር፣ ምክኒያቱም ሌሎችም ዲያቆናት በሥፍራው ነበሩና! ትልቁና ይቅር አይባሌው ስሕተት፣ ያ ዲያቆን ወደ ሎንደን ከተመለሰ በኋላ፣ እራሱ በበተነልን ደብዳቤ፣ "ተገንጥለው ከሂዱት የሥላሴና የገብርዔል ቤተክርስቲያናት ጋር ታርቀን ተመልሰን አንድ እንሁን" ማለቱ ነበር። ያ እንዴት ይሆናል ብለን ተቃወምን። እኔም አባን ከነዚህ ኟሚ-ሻሪዎች (king makers) ለመከላከል በስተመጨረሻ የሚታየውን ማጣቀሻ ጻፍኩ[iv]። አንዳንዴ ከሰው ጋር ቢጋጩም፣ “አባ ግልፈተኛ ናቸው እንጂ ክፉ አይደሉም” እያልን ተሟገትንላቸው። አይ የዋህነታችን! እነዚያ ወጣቶች አካሄዳቸው ለቤተክርስቲያኗ አደገኛ ነበር። እንዳሁኑ ግን አላሰጋትም። አሁን <u>**አባባሱባት**</u>።

# እብድ ቢጨምት እስከ እኩለ ቀን ነው።

የቤተክርስቲያኗ ዕዳ ተከፍሎ ካለቀ በኋላ፣ አባ **ለየት** ያለ ጸባይ ማምጣት ጀመሩ።ቤተክርስቲያኗን በተመለከተ አንዳንድ ክሶች በጠላቶቿ መምጣት ጀምሯል። የውስጥ አዋቂ ተቀናቃኞቻቸው ብለውት እንደነበረው አባ እንደፈለጉ፣ የቤተክርስቲያኗን ገንዘብ **መበደር ከጀመሩ** ሰነባብተዋል። ሥን-ሥርዓት ይኑር እያሉ ቀድሞ የተነሱባቸው ሰዎች የጻፉት፣ ሰዎች ከታጋይ ጳዎሎስ ጋር መተሳሰራቸው ከፋ እንጂ፣ አባን በተመለከተ ያሏቸው ነገሮች ትክክለኞች ሁነው ተገኙ። መተዳደሪያ ደንባችን ያረጀና ከምንኖርበት

አገር ጋር የማይጣጣም መሆኑ ስለታመነ፣ ያንን አርሞ ወደዘመናዊና ቀልጣፋ መተዳደሪያ ነድፈው ለሕዝብ እንዲያቀርቡ፣ አንድ አርቃቂ ኮሚቴ ከተቋቋመ ዓመታት አስቆጥሯል። እሳቸው የማይፈልጉት ሕግ እንዳይረቀቅ ተከላከሉ። ምነው ቢባል፣ የአባን ሥልጣን ይገድባላ! ብዙ ጊዜ የፈጀ ሕገ-ደንቡ በስንት መከራ ተረቅቆ ለሕዝብ ይቅረብ ቢባል፣ አባ "ሕገ-ደንቡ ቤተ ክርስቲያኗን ከካህናት እጅ አውጥቶ "በቦርድ" እንድትተዳደር ያደርጋታል ብለው እሪ" አሉ። አልፈው ተርፈውም፣ ደፍተራ ጓደኞቻቸውን ይዘው፣ ከሌሎች ጥቂት ካህናት ጋር ሆነው ተለዋጭ ሕገ-ደንብ አርቅቀው ከተፍ አሉ። (ለመሆኑ፣ ለደፍተራው በየወሩ £1000 የሚከፈላቸው ምን እየሠሩ ነው?) ግራ የሚያጋባ ነው። እሳቸው ያቀረቡት ሕግ መንግሥት ረቂቅ ውስጥ፣ "የቤተክርስቲያኑ አስተዳዳሪ፣ መነኩሴ መሆን አለበት፣ አስተዳዳሪው እንዳሻው ለካህናቱ ደሞዝም መጨመር፣ ጉርሻም መስጠት ይችላሉ" የሚሉ አንቀጾች ሁሉ ነበሩበት። (እዚህ ጋ ለመለጠፍ ቦት አይበቃም እንጂ፣ በዓለም የተናኘው ኢቶጵያዊ አይቶት ቢዝናና ደስ ባለኝ ነበር)። አንዳንድ "አፍዝ አደንግዝ የተደገመባቸው፣ አሽቃባጭ ሴቶቻቸውና ለጋ ወጣት ዘማሪዎቻቸው፣ "ቦርድ ሊያደርጓት ነው! ቦርድ ሊያደርጓት ነው" ብለው አስተጋቡ። አይ አለማወቅ። ቦርድ ማለት እኮ የተለየ ነገር ሳይሆን፣ በዘመናዊ መልክ የተቋቋመ የሰበካ ጉብኤ ነው! ስሙም "ሰበካ ጉባኤ" እንደተባለ ላይቀየር ይችላል።

የአርቃቂ ኮሚቴው የነደፈውን ረቂቅ ገና ከጠዋቱ ዘመቻ ተጀመረበት። ከዚህ በፊት ከሙሉጌታ አሥራተ ጋር ሁነው ቤተክርስቲያን ካስዘጉን መሪጌታ ጋር ግንባር ፈጥረው ይደቁሱን ገቡ። መሪ ጌታው በየእሑዱ እየወጡ፣ "ከካህን ቃል ከወጣችሁ ትቀሰፋላችሁ" የሚል ሁሉ ስብከት እየሰበኩ ያስቦኩን ጀመር። እንዴ! እሳቸው እግዚአብሔርን ሆኑ እንዴ! መንግስተ ሰማያት የሚገባውናን ገሀነም የሚገባን ወሳኝ ማን አደረጋቸው! ካቶሊኮችስ እንደዚያ ብለው አልነበር ማርቲን ሉተርን የቀሰቀሱ። እኔ እንኳን አባን ከሕዝብ ጋር እንዳይጋጩ እንዳቅሚቲ ለመምከር ሞክሬ ነበር። አሁን እስቃለሁ። አባ ራስፑቲን ከሰው ደኅና ምክር ሊቀብሉ! ያውም ከኔ! እግዚአብሔር ያክብራቸውና በሚያስገረም ሁኔታ፣ "ወንድሙ አንተ የምታምነው በዲሞክራሲ ነው። ቤተክርስቲያን የምትተዳደረው በቴዎክራሲ ነው። አንተ የቤተክርስቲያን ሕግ አታውቅም" ብለውኝ ጥሜን አበረሩት!

መቸም **እብድ** ቢጨምት እስከ እኩለ ቀን ነው እንደሚባለው፣ የአባ ጸባይ እንዳለ ተመልሶ መጣ። አባ በዚህ ተወስነው አልቀሩም። የቤተ ክርስቲያኑን ንበረት በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር ስለነበረ፣ ማንም ሊነቅነቃቸው እንደማይችል ተማመኑ። **የቤተክርስቲያን ንብረትን** ከግለሰብ እጅ አውጥቶ፣ በራሷ እንድታስተዳድረው አመቻችቶ የተረቀቀውን ሕግ ባለመደገፋቸው፣ ሕዝቡ ደግሞ ሕገ ረቂቁን ስለተቀበለው አባ ተበሳጩ። አሁን አሉ ከሚባሉት ትላልቅ የቤተክርስቲያን አዛውንትና ወይዛዝርት ምንም ድጋፍ አላገኙም። የቀሩዋቸው **አንዳንድ ምንም** የማይውቁ ልጆች፣ መዘምራን፣ የተወሰኑ ዲያቆናትና **እንዲሁም አንዳንድ** ወይዛዝርት ጋር ተጣብቀው ቀሩ። ስለዚህ አንድ ኃይለኛ ወዳጅ ማግኘት ነበረባቸው። እሱም ወያኔ ነው። የወያኔን ልብ እንዴት መልሰው ይማርኩ? መቸም ስይጣን **ለወዳጁ**፣ ዕቅድ ነድፎ ያዘጋጃልና፣ ታጋይ ጳውሎስን ገደለላቸው። በዚያ ዙሪያ አንዲት ተንኰል ብልጭ አለችላቸው? ስለሷም ቁጭ ብለው አውጥተው አውርደው፣ "የበሰበሰ ዘናም አይፈራም" እንዲሉ አንድ ጥሩ ቲያትር (ተውኔት - ድራማ) አዘጋጁ። ልክ እንደሰሎሞን ተካልኝ (ቅንድቡ ያማረን አልዘመሩም እንጂ) 180 ደግሪ ዙረው፣ የወያኔን አንጀት ለመብላት፣ ዝግጅታቸውን ፈጸሙ። ዕለቱ እሑድ ቀን ነበር። የወያኔ ደጋፊዎች፣ አባና ሕዝቡ ሆድና ጀርባ መሆናቸው ከተሰማ ወዲህ ቤተክርስቲያኗን **እንደ ዝንብ ወረዋታል። አባ፣ የተውኔታቸው ታዳሚ አገኙ ማለት ነው።** በተውኔታቸው አንድ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንን በሙሉ አንጀት እርር-ድብን የሚያደርግ ድራማ (ተውኔት) ሠሩ። በጣም በሀዘን እንደተመቱ ማቅ ለብሰው ዋነኛው ሀዘንተኛ መስለው ትውኔቱን ተወኑት። ትወናው ደግሞ እንዲህ ነው። እሑድ በጠዋት ገብተው ጽናጽል ይዘው የታጋይ ጳውሎስ ስም ከ፲፱፻፺፪ ዓ.ም ጀምሮ ባልተጠራበት ቤተክርስቲያን ውስጥ፣ አንገታቸውን ደፍተው እንዝርት እንደጠፋባት ሴት እየተንጎዳጎዱ፣ "አ እግዚዖ አዕርፍ ነፍሰ ገብርከ፣ ብጹዕ ወቅዱስ አባ ጳውሎስ!" እያሉ ማጉተምተም ጀመሩ። ነገሩ፣ "አቤቱ ጌታ ሆይ! የባሪያህን የብሱዕ ወቅዱስ አባ ጳውሎስን ነፍስ አሳርፍልን" ማለት መሰለኝ። ያልተጋበዙ እንግዶቻችን፣ ከመቅጽበት መሀረባቸው እያወጡ፣ እንባቸውንና ሌላም መጠራረግ ጀመሩ። የቤተክስቲያኗ አባላት አጉረምርመው "አባ በጤናቸው ነው" ብቻ ብለው ዝም አሉ። እሳቸው ቀጠለቡት። ቅዳሴው ሲያበቃ፣ ማንንም ሳያማክሩ፣ ከተቀሩት ካህናት ጋር ሳይነጋገሩ፣ ለሰበካ ጉባኤው እንኳን ሳያስታዉቁ፣ ልክ ከዚህ በፊት በጀግነነት፣ "የአባ ጳውሎስ ስም ከእንድግዲህ በዚች ቦታ ብጹዕ ወቅዱስ አያባልም" ባሉባት ያልሞተች አንደበታቸው፤ "በሚቀጥለው ሰንበት ለብጹዕ ወቅዱስ አባ ጳውሎስ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ፓትሪያርክ ሙሉ ፍትሀት እናደርጋለን" ብለው አወጁ። <u>ያን ቀን ነበር፣ ከዚያች ከተጎዘጎዙባት የሕዝብ ልብ እንደኪራይ ቤት ጓዝና ጉዝጓዛቸው አዝለው ውልቅ ያሉት።</u> አንድ ታላቅ ጳጳስ ይኽ ጉድ ሲነገራቸው፣ ከት ብለው ስቀው፣ "አይ አለማወቅ! አይ ድንቁርና! ተራ ካህን ሆነ መነኩሴ ለፓትርያርክ ፍትሀት የማድረስ ሥልጣን የለውም እኮ። ለሱ ፍትሀት የሚያደርግ ሥልጣን ያለው ጳጳስ ብቻ ነው። እንዴት ወርደናል!" አሉ። ብዙ ነገር እዚያ አካባቢ ስለማናውቅ ተውነው። ብቻ ሕዝቡ እንደምንም ተባብሮ ያንን አስጣላቸው።

**ምን ያሉ አባት ናቸው፣ ተዝካር የለመዱ**
**አስታርቁኝ ብላቸው፣ ፍታት ብለው ሂዱ**
ደራሲው፡ ሕዝብ

አባ፣ ክፉ ከፋፋይ ናቸው። አሁንም የምንፈራው ይኸንኑ ነው። ካህኑን ከሕዝብ ለማጣላት ብዙ ጥረው ነበር። አሁን ደግሞ ሕዝብን ከሕዝብ ነው ማጋጨት የጀመሩት። ሰው የማከበሩን፣ የታመመን መጠየቁን፣ ያዘነን ማጽናናቱን፣ የተጣላን ማስታረቅማ ጨርሶ ረስተውታል። ጉዳያቸው አይደለም። የእግዚአብሔርን ነገር እርግፍ አድርገው ትተው፣ ጨርሶ ከአንድ መነኩሴ፣ ያውም **ቆሞስ** ይቅርና፣ አንድ ተራ በክርስቶስ የሚያምን ምዕምን እንኳን **የማይጠበቅ** ጸባዮች ማንጸባረቅ ከጀመሩ ውለው አድረዋል። ቁጣ


ቁጣ ይላቸዋል (ቅደም የጠቆምኳችሁን፣ የኮማንደርን አሰፋ ጽሑፍ አንብቡ)። ከሁሉ ከሁሉ፣ የሚከራከሯቸውን ለማሸነፍ፣ ዓይን ያወጣ ውሸት ሁሉ መስቀል ይዘው ሲዋሹ ትንሽም አይሰቀጥጣቸውም። ጉድ እኮ ነው። ይኽ ጸባይ በፊት ታምቆ ባይኖር አሁን ከየት መጣ? ያልነበረማ ከይት ይመጣል፣ አፍነው ቀብረውት ነው እንጂ! አንድ ወንድሜ እንዲህ አለኝ። ሰይጣን ህጃውን ሊያሙላ ሲከጃጅል፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቃቅሳል።

አንድ አባት አሉኝ። ከሊቅም ሊቅ ናቸው። ቄስ ወይም መነኩሴ ግን አይደሉም። ስለቤተክርስቲያናችን ግን ማንም ሊቅ ነኝ የሚል አይደርስባቸውም። የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ናቸው። እኔ በፈለግኳቸው ጊዜ ላገኛቸው ስለምችል፣ ጥቂት በጣም ከታደሉት መሀል አንዱ ነኝ። በተረበሸኩ ቁጥር ኢ-ሜል እንለዋወጥና ወይም እንደዋወልና ያረጋጉኛል። ካህን ነን ባዮች የአቡነ ቴውፍሎስን መገደል መደገፋቸውን የገለጹበትን ደብዳቤ ልኬላቸው፣ አሁን አባ እዚህ ሎንደን ሕዝቡን እንደሚያምሱት ምርር ብዬ ስነግራቸው፣ በኢ-ሜል እንዲህ አሉኝ። "They know the rituals but apparently not the spirituality." ቃናውን እንዳላበላሸው፣ አልተረጉመውም።

# እጸድቅ ብዬ ባዛላት ተንጠልጥላ ቀረች

ወቸ ጉድ! ተቀምጠው የሰቀስሉት ቁሞ ማውረድ ችግር ሲሆን ምን ይባላል! አባ ሕዝቡ "እጸድቅ" ብሎ፣ ከመረጣቸው በኋላ፣ "ሹመቴ ከእግዚአብሔር ነው። **ወግድልኝ**!" ብለውት አረፉ። "ከሶስት ዓመት በኋላ ሕዝቡ ከፈለገዎት ይቀጥላሉ፣ አለበለዚያ በሰላም ይወርዳሉ" የተባሉት ሰውዬ፣ "የለም እግዚአብሔር ነው የሾመኝ፣ እግዚአብሔር ነው የሚያውርደኝ" አሉን።" "እኔ የማምነው በቴዎክራሲ እንጂ በዲሞክራሲ አይደለም" ብለው አፍ አውጥተው ነገሩን። ሶስተኛውም፣ አራተኛውም፣ አምስተኛውም፣ **ስድስተኛውም፣ ዓመት** መጥቶ አለፈ። **ሰባተኛውንም** አገባደናል። በተለያዩ ሰንካላ ምክንያቶች አባ ምርጫውን በሥነ-ሥርዐት ለማካሄድ ፈቃደኛ አልሆኑም። ከምዕምኑ መሀል የተመረጡት የሰበካ ጉባኤው አባላት ስልችት ብሎአቸው ሁሉንም ለአባና ለአንድ ደንገጡራቸው ትተው ቤታቸው ቁጭ ብለዋል። አባ ሕዝብ ካልፈለጋቸው በሰላም መውረድአቸው ቀርቶ የመረጣቸውን ሕዝብ የተገላቢጦሽ በጉልበት ሊያወርዱ ታጥቀው ተነስተዋል። አንድ ለዚህ የሚስማማ ግጥም ነበረኝ። ርዕስም "ጭራሽ?" ነው። የተጻፈውም መስከረም ፲፱፻፺ ዓ.ም ነበር። ከመሀል ከነበሩት ስንኞች እንዲህ የሚል አለ።

እስከዚህ ጥቃቱ፣ ውርደቱ ካልበቃን
አዚሙ እንዲለቀን፣ ከእንቅልፍ እንዲያነቃን
ያቃጥለን ያንድደን፣ ይፍጀን እንደ ረመጥ
አናሳው ይፉንን፣ ይቀጥል ማላገጥ


Re'ese Adbarat St. Mary of Debre Tsion Ethiopian Orthodox Tewahedo Church, London

Date: 4th March 2013
DTM-597-Ext METP--00597/13

Mr Getachew Beshahwred
Mr Mamo Lema
Mr Teshome Seifu
Mr Girma Telila
Mr Hailu Tibebu
Mr Meku Getachew
Mr Asrat Yigletu
Mr Abebe Tolossa

Mr Andebet Kassa
Mr Dawit Gessesse
Deacon Mahder Kassa
Mr Yakob Ashenafi
Mr Alebachew Desalegn
Mr Teferi Mamo
→ Mr Tilaye Yeshanew

Re: **Barring from the Premises of the Church: St Mary of Debre Tsion Ethiopian Orthodox Tewahido Church**

As part of our responsibility to the congregation of St Mary of Debre Tsion Ethiopian Orthodox Tewhido Church and our obligation to the Charity Commission, the trustees would like to ensure the safety and peace of the community who come to the premises for worship.

However, in the past few months you have been responsible for number of disruptions of meetings, by jeering, shouting and showing threatening behaviour and disregard to the sacred place of worship.

These unconstitutional, unethical and anti-canonical behaviour reached to shocking climax on Sunday the 3rd of March 2013 where you disrupted the Holy Communion Service, shouting inside the church building holding placards and using handheld Megaphone, which required the attendance of about 25 police officers in order to restore peace.

As Trustees we have responsibility to ensure the security of the church assets, the safety of the congregation including children, infirm and vulnerable adults as well as the peace and tranquillity of the wider neighbourhood.

Therefore, your membership right to enter the church premises has been suspended until the matter is dealt legally and is resolved peacefully.

We strongly **advice you not to ignore this decision!** If you ignore this decision and act against this decision, you will be held responsible for any problem created due to your presence.

Thank you for your cooperation,

The Trustees of
Re'ese Adbarat St Mary of Debre Tsion
Ethiopian Orthodox Tewahedo Church

CC: Charity Commission
Metropolitan Police

St Mary of Debre Tsion, Ethiopian Orthodox Tewahedo Church, 1 St Philip square, Queenstown Road, Battersea, London, SW8 3RT
*Registered Charity No: 1060394.*

እንዲያውም ጭራሹን፣
ዓላማው **እንዲሳካ**
ሰላም እንዲናወጥ
ለአጤ በጉልበቱ፣ እንዲመቸው መርገጥ
"በቲዎክራሲ"፣ በአዲሲዮው ፍሊጥ
አሁንስ ምን ቀረው፣
ሕዝቡ ይበተንና፣ አዲስ ይመረጥ

አባብሰውባት፣ ሕዝቡን በትነውታል። እሳቸው ኮቴአቸው ከአዲስ አበባ ሳይነሳ፣ ቤተክርስቲያናን በእግሯ ያቆሟትን አዛውንት ለማጥፋት ያልሞከሩት አድማ፣ ያልሸረቡት ገመድ፣ ያላቀዱት ሸር አልነበረም። ሕዝብ መርጦአቸው፣ **ከተለያዩ** ኮሚቴ ከተውጣጡ አባላት ላይ ዘመቻ ከጀመሩ ውለው አድረዋል። በስተመጨረሻ በሥልጣናቸው፣ ቤተክርስቲያኗ ስትገዛ ዋልታና ማገሯ የነበሩትን ዋና ዋና ጎበዝ ሰዎችን ጨምረው፣ **አሥራ አምስት** የቤተክርስቲያኗን አባላት በሥልጣናቸው "እዚች ግቢ ትደርሱና፣ በፖሊስ እያዳፋኋችሁ፣ እያስቀጠቀጥኳችሁ አሳስራችኋለሁ" የሚልደብዳቤ ጻፈው፣ በቤትክርስቲያኗ ማህተም አትመው፣ ፈርመው፣ በቤትክርስቲያኗ ገንዘብ፣ **ለእያንዳንዱ** ብዙ ፓወንድ ከፍለው በሪኮማንዴ ፖስታ በያድራሻቸው ላኩ። ድብዳቤው ስካን ተደርጎ በ-ኢሜል ለያንዳንዱ አባል ተልኮ ስናየው፣ ደነገጥን። እ!!! አባ እዚህ ደርሰዋል! ከዚህ በፊት "ይኽ ሕገ-ደንብ ተረቅ ሥራ ላይ የሚውለው ሬሳዬ ላይ ነው" ብለው የዛቱትን **ዛቻ፣** እግዚአብሔርንም፣ ሰውንም ሳይፈሩ ተግባራዊ አደረጉት። ወይ አባ ጉልቤ (bully)! በጠቅላላ፣ ሕዝብ የመረጣቸውን መተዳደሪያ ደንብ አርቃቂዎቹን፣ በአንዲት ብጣሽ ወረቀት አባርረው አረፉ።

“ቀሚስ ብለብስ ሴት መሰልኳችሁ!” ያሉትን ሥራ ላይ አዋሉ። ሕዝቡ ተረበሸ። ተቆጣ። ዳሩ ግን፣ ቁጣውን ለጊዜው ትቶ፣ ለማንኛውም ዕለቱ አቢይ ጾም የሚያዝበት እሑድ ነበርና፣ በሰላም አስቀድሶ ሁለቷን ወር ሱባዔ ገብቶ የሎንደኑን አባ ራስፑቲንን ከፋሲካ በኋላ ሊጋፈጣቸው አስቦ ወደቤተክርስቲያን ሲሄድ፣ አባ ሆዬ፣ የወያኔ ኤምባሲ ሰላማዊ ሰልፍ ሲኖርባቸው፣ በእስፖርት ሰውነታቸው የዳበረ ወጠምሻ በር ጠባቂ ከሚከራይበት ልዩ ድርጅት፣ እንኳን ሰው ነክተው በዓይናቸው ሲገላመጡ ሊበሉህ የሚደርሱ ጠብደሎች ዘብ አቁመው ጠበቃቸው። ወጠምሾቹ የሰኩሪቲ ዘበኞች፣ የአባ ራስፑቲን ደንገጡሮች ከስር-ስራቸው ሁነው “ይኸን አስገባ፣ ይኸን ከልክል” እያሉ **የአባን** *መመሪያ* **መስጠት ጀመሩ፣** አንዲት ቆራጥ እህት ደንገጡሮቹንም፣ ወጠምሻዎቹንም አልፋ ገብታ ስለነበር፣ አባ ጉልቤው (ቡሊው) አገር ደኅና ነው ብለው፣ **የክልከላ** ***መመሪያ*** **ሰጥተው ተዝናንተው ክርስትና** ሊያስነሱ፣ ሊያጠምቁ ሲንጎዳጎዱ ደረሰችባቸው።ያኔ ያለ የሌለውን ኃይሏን ተጠቅማ ቤተክርስቲያኑን በጩኸት አናጋችው። በፊትም በንዴት ቋፍ ላይ የነበሩ ምዕምናን፣ ወጠምሻዎቹን ብድግ አድርገው ወደጎን አሽቀንጥረው፣ ደንገጡሮቹን በታትነው በሩን በርግደው ገቡ። አባ ጉልቤው ዓይናቸው ፈጠጠች። ሩጠው ቅድስተ ቅዱሳት ታቦቱ ጋ ገቡ። ሕዝቡ፣ ቅድስተ ቅዱሳኑን ቦታ በማክበሩ ነው እንጂ፣ አንዲት እናት ከዓመት በፊት ለአባ እንደተነብዩላቸው፣ ያ የተናደደ ሕዝብ እንደጋዳፊ መሬት ለመሬት እየጎተተ ባወጣቸው ነበር። ክርስትናው ተቋረጠ። ቅዳሴው ሳይጀመር ቆመ። ምድሪቱ ቀውጢ ሆነች። የሳቸው ደንገ-ጡሮች ተንጫጩ። “ምንስ ቢሆን ምንስ፣ ቤተክርስቲያን በጦም ምድር እንዴት ትበጠበጣለች” አሉ። ፍቅር ዕውር ነው ማለት ይኸ ነው። እንኳን ለዳግማዊ ራስፑቲን እና፣ ለላካቸው ለታጋይ ጳውሎስም ያልተበገረው የሎንደን ምዕምን እንደገና ተአምር መሥራት እንደሚችል አረጋገጠ። ፖሊስ እየተንጋጋ መጣ።

በሚቀጥለው ዩ-ቲይብ እንደሚታየው፣ አቅላቸውን ጥለው የሚንጫጩት የራስፑቲን ደንገጡሮችና ያልበሰሉ መዘምራን ናቸው፡ አዛውንቱን የሚሰድቡት። አብዛኛው ሕዝብ፣ ቤተክርስቲያኑን በርግዶ ከገባ በኋል በነሱ ጫጫታ ሳይደናገር፣ “ኃይል የእግዚአብሔር ነው” የሚለውን መዝሙር እየዘመረ ቁጭ ብሎ ተገኘ። http://www.youtube.com/watch?v=TC2_T3j5JyU በፊልሙ ላይ እንደሚታየው፣ አንዷ የአባ ራስፑቲን ደንገጡር፣ “I am Woyyane! Yes I am Woyyane” እያለች እንደ አልጀዚራ የጦር ሜዳ ሪፖርተር በእንግሊዝኛ ስትንጣጣ፣ በዕሜ የገፉ ወይዘሮ ደግሞ እናቷ ሳይሆኑ አይቅሩም፣ “እንዴ! ወያኔማ ሊሰደብ አይችልም! ወያኔ ጦርነት አሸንፎ፣ አገር የሚገዛ ታላቅ መንግሥት ነው!” እያሉ፣ አዶ ከርቤ እንደያዛቸው አጓሩ። ፓሊስ ይኸን ሁሉ ጉድ ያያል። ረበሹ የተባሉት በሰላም ቁጭ ብለው በሥርዐት ይዘምሩ ነበር። ተረብሸን ብለው ፖሊስ የጠሩት ግን አብደው ጨርቃቸው ሊጥሉ ትንሽ ቀራቸው። የትኞቹን እናውጣላችሁ ብለው የጠራቸውን የአባን ቲፎዞ ቢጠይቁት ጣቱን በሰላም ወድተቀመጡት ብዙ ሕዝብ እያሳየ “እነሱን አለ!” ፖሊሶቹ፣ ሕዝቡን ሳይሆን ትቂቱን የአባን ሥርዐተ ቢስ ጀሌውችን ማስወጣት እንደሚቀል ተረዱ። “ይህን ሁሉ ሰው፤ ማሰወጣትም ማሰርም አንችልም” አሉ። ቤተ ክርስቲያኗን ከእዚህ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ላይ እንድትደርስ ያደረጉት ባለሙያዎች፤ የእመቤታችን አገልጋዮች የሆኑ የምዕመናን ተወካዮች (አሁን በአባ ከቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ እንዲወገዱ ትዕዛዝ የተላለፈባቸው)፤ በጥሞና ሕዝቡን ወክለው ለፖሊሶቹ ነገሮችን እያብጠረጠሩ ሲገልጡላቸው፣ ችግሩ የት ጋ እንደነበረ ገባቸው። አባ ከተቀርቀሩባት ከቅድስተ ቅዱሳኑ እየተምዘገዘጉ ሲመጡ፣ ፖሊሱ ከዚያ ዞር እንዲሉ ሲያስጠነቅቃቸው፣ አፍረው ተመስለው እዚያችው ተወሸቁ። ፖሊስ ነገሩን ተረዳ። እንዴት በሕግም ሕዝቡ መብቱን መጠበቅ እንዳለባቸው መከራቸው። (አንባቢ መረዳት ያለበት ጉዳይ ቢኖር፣ ከባድ ችግር አጋጥሞኝ ቤተክርስቲያን መሄድ ባለምቻሌ፥ ከሩቅ ሁኜ ደቂቃ በደቂቃ የምትፈጽመውን ሁኔታ ያለማቋረጥ በስልክ መከታተል ችዬ ነበር። በትዕግሥት ተራ በተራ እየተቀባበሉኝ ያንን ሁሉ እንድከታትል የረዱኝና በዓይኔ የማላየውን ከስተት ለገለጹልኝ ከልብ አመሰግናለሁ።)

ጊዜው ገሠገሠ። ሕዝቡ ምግብ ሳይቀምስ እዚያችው ደርቆ ዋለ። ፖሊሱ ወደየቤታችሁ ሂዱ ብሎ ሕዝቡን ቢሚጸን፣ መብታቸውን የገፈፉት አባ ተብዬው አመጸኛ ሰው ከዚያች ቅዱስ ቦታ ለቀው እስከሚወጡ አንነቃነቅም አለ። ቁልፍ ያስረክቡ ተባለ። አባ ራስፑቲንን “ውጡ” ቢባሉ፣ ማን ከቅድስተ ቅዱሳን ጎትቶ ያስወጣቸው? ቀኑ ሲገባደድ ፖሊሱ ለቀው እንዲሄዱ ቢመከሯቸውም እምቢ አሻፈረኝ አሉ። በመጨረሻ ግን የሕዝቡን ቆራጥነት ሲያዩ ወጥተው ሹልክ ብለው ሄዱ። ሕዝቡም ደስ አለው። አባ አይመለሱ በዚያው ይቅሩ አለ። ፖሊሶቹ ከተቀሩት የአባ ተከታይ ካህናትና ሕዝቡ መሀል ሰላም እንዲኖር ሞከሩ። ቁልፉ ለአንድ ወጣት ቄስ ተሰጠና እሱ ቤትክርስቲያኑን እንዲዘጋ ተስማሙ። ቄሱ ግን በአባ ራስፑቲን ድግምት ሥር ስለነበረ ይመስላል፡ “ቁልፉን የምይዘው ለአሁን ብቻ ነው። ቁልፉን መልሼ ለአባ ነው የማስረክበው” አለ። ፈሪ ፍርፋሪ! ሕዝብ ያዋጣው ነበር! ለማንኛውም ፖሊሶቹ፣ ሁለት ከሕዝብ ወገን፣ ሁለት ከአባ አማካሪዎች አስመርጠው፣ ድርድሩ ወደፊት በጾሙ ወራት እንዴት መቀጥል እንደሚቻል ለመነጋገር ማክሰኞ እንዲገናኙ አስማምተው ሕዝቡ ወደየቤቱ ሊሄድ ቻለ።

ማክሰኞ ደረሰ። ሕዝቡም ጸሎቱን ሊያደርስ፣ ከሕዝብ ወገን የሆኑ ሁለቱ፣ ከአባ ወገን የተሰየሙትን በቀጠሮአቸው መሠረት አግኝተው ለመደራደር ወደ ቤተክርስቲያን ጎርፉ። ወደ ቅጥር ግቢው ሲገቡ፣ ያልተጠበቀ ነገር ገጠማቸው። አባ የእግዚአብሔር ሳይሆን የሰይጣን አገልጋይ ስለነበሩ፣ ሕዝቡን በጾም ምድር መስገጃ ቦታ አሳጥተውት አረፉ። ይኸውና፣ በስተመጨረሻ ከሰይጣን እንቅፋት በጾም በጸሎት፣ ከወያኔ ሽር በቆራጥነትና በአርበኝነት ቤተክርስቲያናችንን እንዲጠብቋት፣ የተረከቡ ባለአደራ መነኩሴ ነኝ ባይ ሀሳዊ ደብረ-ብጥብጥ፣ አንገት ደፍተው ገበተው፣ ለገንዘብና፣ ለሹመት ሲሉ ጭራሹን የክርስቶስን መንጋ በትነው፣ እስከነ አካቴው የመንጋውን መሰብሰቢያ የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ዘግተዋት ሜዳ ላይ በትነውት አረፉ! አቤት እግዚዖ!

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 21 ከቁጥር 15 እንዲህ ሲል ለካህናቱ፣ ለዕውነተኞቹ እረኞቻችን አስረክቦን ነበር።

*“የዮና ልጅ  ስምዖን ሆይ፣ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? አለው። አዎን ጌታ ሆይ፣ እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ አለው። ግልገሎቼን አሰማራ አለው። ደግሞ ሁለተኛ፤ - የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ትወደኛለህን? አለው። አዎን ጌታ ሆ፣ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው። ጠቦቶቼን ጠብቅ አለው። ሦስተኛ ጊዜ፣- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ትወደኛለህን አለው። ሶስተኛ ፣ - ትወደኛለህን ስላለው ጴጥሮስ አዘነና፤ - ጌታ ሆይ፣ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፣ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው። ኢየሱስም፤ - በጎቼን አሰማራ አለው።”*

አቤት አቤት የክርስቲያን አምላክ ይኸን ጉድ ታያለህ! እንግዲህ፣ ጠቦቶቹ ሕጻናት ናቸው። ግልገሎቹ፣ ወጣቶች ናቸው። በጎቹ እኛ ነን። እዩንማ ሜዳ ላይ እርኛ እንደሌለን በጎች ተበትነን! ቀበሮው ጦቦቶቹን ሊነጥቅ፣ ጅቡ ግልገሎቹን ሊመነትፍ፣ አንብሳው በጎቹን ሊውጥ በዙሪያችን እየጮኸ፣ እያስካካ እና እያገሳ ይንጎማለላል። እረኞቻችን በረታችንን ቆልፈው የት ገቡ!!! ካህናት ሆይ! ከነዚህ የጌታ በጎች አንዲት ነፍስ እንኳን ብትጠፋ ጌታ ከእናንት እጅ ይሻታል። አላወቅችሁም?! ዳሩ ምን ታውቃላችሁ። መጽሐፍ ቅዱስን ጥርት አድርጋችሁ ብትማሩ ኑሮ፣ የሚከተለውን ጽሑፍ ጽፋችሁ ባለፈው ሳመን ጥሪአችሁ ባልበተናችሁ ነበር።

> “ቤትክርስቲያን ከክርስቶስ አካልነት ወጥታ የግል ድርጅት (Company) አካል (Incorporated) መሆን አለባት? ፍጹም ክህደት ነው። የለባትም። (ኤፍ 5፡23)"

ጳውሎስ ግን በዚያ ጥቅስ የሚለው፤ “ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ፣ ለባሎቻችሁ ተገዙ። ክርስቶስ ደግሞ የምቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ፣ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና።”ታዲያ **ይህንን** የጻፋችሁት፣ መጽሐፍ ቅዱስ **በየቤታችን** እንዳለን ባለማወቅ ነው ወይስ የማናነበብ ችግር ያለብን መሀይምች **መስለናችሁ**?። የባልና ሚስት ጉዳይ ከኮምፓኒ ጋር ምን **አገኛኘው**?  ኮምጨ አምባው እንዳለው፣ መሀይም ላሉን፣ መሀይም እናንተ፣ መጽሐፍ ቅዱሱን እንኳን በቅጡ የማታውቁ!

አሁን የምንሰማው፣ የሎንዶኑ ራስፑቲን ቁልፍዋን **ለአቡነ እንጦስ ሊያስርክቡ** እየተደራደሩ እንደሆነ ነውᵛ። መረጃውን ከግርጌው በተለጠፈው ድረ-ገጽ ማየት ይችላሉ። ከፈርዖን የበለጠ ጨካኝ ሁነውባት ሁዳዴ ጾም በገባ **ማግስት፣ አባ ቤተክርስቲያኗን ጠርቅመዋ**ት ከሥፍራው መሠወራቸው፣ በምንም ዓይነት የክህነትን ትርጉም የማያውቁ፣ ሳይበቁ የመነኑ አባት ያስመስላቸዋል። አንዴ፣ እንዲሁ ታጋይ ጳውሎስ ሲረብሹን እንዲህ የምትል ስንኝ ቋጥሬ ነበር።

ሹመት በማዕረግ እየገነኑ
በስልጣን ጥማት እየባዘኑ
አባ ዲያብሎስ ሰይጣኑ
ምነው ሳይበቁ መነኑ?

ማንኛውንም ዓለማዊው ሰው የሚሠራውን ሸር እየሠሩ "መንኩሼአለሁ” ላሉን፣ ለዘመኑ ራስፑቲንም ትሆናለች። ቤተክርስቲያን የሚዘጋ፣ ዲያብሎስ ያደረበት ብቻ ነው። እንግዲህ እኚህ ናቸው፣ “አባት በሉኝ፣ መልአከ ጽዮን በሉኝ፣ ቆሞስ በሉኝ” እያሉ ሲያታልሉን የኖሩ! ከላይ አክሴማ የለበሱ የመነኩሴ መሳይ ከውስጥ ግን እልም ያሉ የዓለም ሰው ሆነው ተገኙ! ሕዝቡ ተስፋ ሳይቆርጥ፣ አባ ራስፑቲንን በድንብ ሳያቃቸው ቀርቶ፣ ልባቸው ድንገት ራርቶ ለጿሚው ኢትዮጵያዊ ቤተክርስቲያን በሰንበት ዕለት ይከፍቱ እንደሆን ብሎ ግልብጥ ብሎ ሲሄድ የሚከተለው ማስታወቂያ አፈጠጠበት።



አባታችን እያልናቸው፣ ፍቅራችንን እየቸርናቸው፣ በረቱ ተዘግቶበት የተበተነ መንጋ አድርገውን አረፉ አይደል ጎበዝ! አይ ክፋት! አረመኔዎችስ ምን ከዚህ የከፋ ሊያመጡብን ኑሯል! በሑዳዴ ጾም ገንዘባችንን ከስክሰን (ከነድሳቱ £1 850 000) የገዛነውን ቤተክርስቲያናችንን ሲዘጉብን ዝም ብለን እንደተበተን እንቅራ! ሙተናላ! ወይ ነዶ! አሁንማ መሄጃ የለንም። የት ሂደን ነው የምናስቀደሰው! የት ሂደን ነው ሥጋ ወደሙን የምንቀብለው! የት ሂደን ነው ልጆች ያሉን ክርስትና የምናስነሳው? የሚጋቡትስ ወጣቶች የት ሂደው ጋብቻቸውን በክርስትና ሥነ-ሥርዐት የሚፈጽሙት? እዚህ ላይ “ምን አገባኝ” ማለት አይቻለም።



አሁንስ ተንገላታን። ግፉ በዛ። ጫን ያለው መጣ። አባባሱባት! የጌታ ታናናሽ ልጆች እንዳለን በአባ ተሰናከልን! የት እንሂድ! እሪ ወደ ጌታ እንበል። ተስፋው የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 17 ቁ2 ላይ እናገኛለን።

> “መሰናከሉን ለሚያመጣው ወይለት! ከእነዚህ ከታናናሾች አንዱን ከማሰናከል ይልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባህር ቢጣል ይጠቅመው ነበር።”

ወየውልዎት አባ! ወየውልዎት!

እግዚአብሔር መቸም ልጆቹን ሜዳ ላይ ሲጥል ያለጠባቂ መልዓክ አይተውም። እሑድ ዕለት ልክ ከዚህ በፊት እነሙሉጌታ አሥራተ ካሳ፣ ሊቅ ካህን ብርሀኑ ገብረአማኑዔል፣ አሁን የአባ አማካሪ የሆኑት ደፍተራው መሪጌታ፣ የግሪን ፓርኳን ቤተክርስቲያን ዘግተውብን ሜድ ላይ ተበትነን ዝናብ ሲቀጥቅጥን፣ በመሀላችን ተገኝተው በጸሎት ያበረታቱን፣ <u>የሕዝብ ወገን ቄስ፣</u> አንድ እሑድ ዕለት፣ የዝናብ ዶፍ እየወረደባቸው፣ አንድ ጃማይካዊ ቄስ፣ አንድ የሕዝብ ወገን የሆነ መሪ ጌታ እና አንድ በወንጌል ትምህርት የተካነ መምሕር ይዘው በሕዝቡ መሀል ተገኝተው፣ ቡራኬ አድርሰው፣ ጸልየው ትምሕርትም ሰጥተው አበረታተውታል። እየሱስ ክርስቶስ ይኸን ውለታቸውን ለሁለተኛ ጊዜ ለቅጣትና ለምሕረት ሲመጣ አራቱን የሰው መላዕክቶቹ ከጽድቅ ቆጥሮላቸው ከቀኙ ያቁምልን። እኛንም በጎቹን፣ እፊቱ ቀርበን ስለነዚህ እረኞች ለመመስከር ያብቃን አሜን!

ባለፉት ሁልት እሑዶች አማላኩን ሊያመሰግን ሂዶ ያለ እረኛ ሜዳ ላይ የተጣለውን መንጋ አስገርመዋቸው የአካባቢው ኗሪዎች በመስኮታቸው እየወጥ ሲመለከቱ ነበር። ቁልፍ የጠፋብን መስሎአቸው ይሆናል። ኢሳት ቴሌቪዥን በቦታው ተግኝቶ እንዲህ እንደሚከተለው ዘግቦት *ነበር።*

http://www.youtube.com/watch?feature=player_embedded&v=1GuaJRLuKvQ

ኢሳት፣ “እኔ ምን አገባኝ” ሳይል፣ ሪፖርተሮቹን በዚያ ብርድ ልኮ ሁኔታውን በመቅረጹ እናመሰግናለን።

በሁሉቱም እሑዶች፣ ዓይን አዎጣዎቹ የአባ ደንገጡሮች፣ ሕዝቡ እንደሚሰበስብ አውቀው አዛውንቱን ለማንጓጠጥ ተገኝተው ነበር። ሕዝቡ ስድባቸውን ሁሉ በትዕግስት ችሎ ጸሎቱን በነበሩት ካሕናት አመራር ማድረስ ችሏል። ሕዝብ አክባሪው ካህን አንድ ላይ ሁነን እግዚያብሔርን እናምልክ ብለዋቸው ቢማጸኗቸው፣ ሊያዋርዷቸው ሞክረዋል። የእጃቸውን ይስጣቸው።

አንድ ወንድም፣ በዚህ መልክ ነበር የነበርውን ሁኔታውን በዘምኑ ቪዲዮ መቅረጽ-ሥዕል የተከታተለው።

https://www.youtube.com/watch?v=wPjnurSvhZ4

# እንጨርስ!

አንባቢ ሆይ! ሎንደን ላይ ከፋት ወንድሞቻችሁንና እህቶቻችሁን በዚህ በዓቢይ ጾም ሰሞን መስገጃ ቦታ አሳጥቶ እያንገላታው ነው። ሕዝቡ አንጡራ ሀብቱን ለውያኔ ወኪሎች፣ በተለይ ለአባ እንጦስ እንደማይሰጥ ያረጋግጥላችኋል። እናንተ ግን፣ የጌታ ጸጋ ከወንድሞቻችሁና ከእህቶቻችሁ ጋር እንዲሆን በያላችሁበት ሱባዔ ግቡለት። “እኔ ምን አገባኝ” አትበሉ።

ግራም ነፈሰ ቀኝ፣ አባና አጋሮቻቸው ማውቅ ያለባቸው ነገር አለ። አንድም የጌታን በግ አንገላቶ ከክፉ ሞት የተረፈ እንኳን የካህን አምባ ገነን ጠብመንጃ የያዘም የለም፣ አይኖርም። እግዚአብሔር ትላንትም ጌታ ነበር፣ ዛሬም ጌታ ነው፣ ነገም ጌታ ነው። ታጋይ ፓውሎስም ሳይናዘዙ ሞተዋል። ጌታ ደግሞ በእናቱ ስም የተጠራችውን ቤት እንኳን ከእንደ አባ ዓይነቱ ዕምነተቢስ እልኸኛ፣ ከዋናው ዲያብሎስም አስጥሎአታል። ታጋይ ጳውሎስ ያልቻሉትን ሕዝብ የትላንት ተላላኪያቸው ሊያንበረክኩት አይችሉም። ቤተክርሲያናችንን ቆልፈው በጾም ምድር መንጋውን ሜዳ ላይ መጣላቸው አንገታቸው ላይ ውፍጮ ታሥሮ ወደ ባሕር ቢወረውሩ ይሻላቸው ነበር። እኛን ታናናሾቹን አሰናክለውናላ! ለወያኔ ቁልፉን ለማስረከብ የሚያደርጉትን መፍጨርጨር በተጠንቀቅ እንጠብቃለን።

አባብሰውባታል! ቤተክርስቲይኗን ዓይናቸው እያየ በእልህና በድፍረት ለእንዲህ ዓይነቱ ብጥብጥና ውጥንቅጥ ዳርገዋታል። ቤተክርስቲያኑን ዘግተው ሕዝቡን በትነዋል። እግዚአብሔር ይኸን ሁሉ ግፍ ያያል! ሕዝቡን ይጠብቃል! እርስቱንም ይባርካል! ታናናሾቹን ላሰናከሉት ግን ወይውላቸው! ይኸ ሁሉ ግፍ እየታየ “ምን አገባኝ” ማለት አይቻልም። ሁላችንም ለሙብታችን ስናል፣ አባ በተንኰላቸው ከፋፍለው ሳያባሉን፣ ጸልየን በአንድ ላይ መነሳት አለብን። ኃይል የእዚአብሔር ነው።

ተረት ልንገራችሁ። አንድ እረኛ ነበረ። ደሞዙንም የሚያገኘው ከመንጋው ባለቤት ነበር። ገና በወጣትነቱ ለዚያ ጌታ ብቻ ሊያደር እራሱን በፈቃዱ ለይቶ ነበር። ከጌታው ጋር ውል ገቦቶ ነበረ። በውሉም መሠረት የመንጋው ባለቤት እንዲህ ይላል። “ደመወዝህን እንደከፍልህ ከፈለግክ፣ በል እንግዲህ ንቃ! በጎቼን ሊነጥቁ ተኩላዎች አሰፍስፈው ተኰልኩለዋልና አትዘናጋ። ጠቦቶቼን አሠማራ፣ ግልገሎቼን ጠብቅ፣ በጎቼን አሠማራ።” እረኛው ግን ከመንጋው ባለቤት ጋር የገባውን ውል ረስቶ ቁማር ጨዋት ገባ። በጎቹ ተረሱ። በቁማሩ ጨዋታ ተበላ። ተናደደ። አኮረፈ። የበጎቹን ማደሪያ በረት ቆልፎ ሂደ። በረቱም የሱ አልነበረም። በጎቹም የሱ ንብረት አልነበሩም። የጌታው ናቸው። በጎቹ በራሳቸው ሣራቸውን ከየቦታው ለቃቅመው በልተው፣ ውሃቸውን ካገኙበት ጠጥተው፣ ሲመሽ ወደለመዱበት ማደሪያ በረት ማንም ሳይሰበስባቸው በራሳቸው መጡ። በረቱ ተዘግቶ ጠበቃቸው። ሜዳ ላይ ፈሰሱ። ጊዜው መሽቷል። መሄጃ የላቸውም። ተቅበዘበዙ። ቀበሮዎቹ ጠቦቶቹን፣ ተኩላዎቹ ግልገሎቹን፣ አንበሶቹ በጎቹን ለመንጠቅ ቋምጠዋል። ጌታው በጎቹን ሊቆጥር ሲመለስ፣ አንዷት እንኳን ከጎደለች ለዚያ ቁማርተኛ እረኛ ወየውለት!

እስከአሁን በትዕግስት ለተከታተላችሁ አንባባዎቼ የምትከተለውን ግጥም እተውላችኋለሁ።

> “እኔ ምን አገባኝ” የሚሉት ሐረግ፣
> እሱ ነው ሃገሬን ያረዳት እንደ በግ፣
> የሚል ግጥም ልጽፍ፣
> ስሜት አንዘርዝሮኝ ብድግ አልኩኝና፣
> “ምን አገባኝ” ብዬ ቁጭ አልኩ እንደገና ።
>
> ኑረዲን ዒሣ

---

i http://www.ethiomedia.com/addis/debre_tsion_church_crisis.pdf

ii http://ecadforum.com/2011/02/26/aba-paulos-and-london-debretsion-wondimu-mekonnen-london/

iii http://wondimumekonnen.blogspot.co.uk/2010/12/blog-post.html

iv http://ethiopia.ecadf.netdna-cdn.com/wp-content/uploads/2011/02/Tagay-Gebremedhin-and-London-Debretsion.pdf?c8b0b4

v http://www.ecadforum.com/Amharic/archives/6553